# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ደ/መዊዕ ቅ/ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን  አመሠራረት ፤ በኔዘርላንድ

## ክፍል አንድ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፤ ቀደም ብለው በተለያየ ምክንያት ወደ ሆላንድ አገ ር በመጡ ካህናትና ምእመናን አስተባባሪነትና ብርቱ ጥረት ፤ ከ1990 ጀምሮ መንፈሳዊ አገልግሎቱን መስጠት ጀመረ ።

እ.አ.አ. ከ1992 ጀምሮ በሆላንድ አገር የስደተኞች ቁጥር እየተበራከተ በመምጣቱና በወቅቱ በነበሩት ዲያቆናት ማለትም ዲ/ን ከፈለኝ ወ/ጊዮርጊስ (በኋላም ቀሲስ) ፣ ዲ/ን ያሬድና ዲ/ን ተረፈ አስተባባሪነ ት የጉባዔው ተሳታፊዎች ባደረጉት ጥረት የመጀመሪያው የስቅለት በዓል በአምስተርዳም ከተማ ፤ እ ንዲሁም የትንሳኤ በዐል በዴንሃግ ከተማ ከጀርመን በመጡት በቀሲስ ዶ/ር መርዓዊ እና በዲያቆናቱ ከተከበረ በኋላ ፤ ምእመኑ እምነቱን እንዲያስፋፋና የበለጠ እንዲጠናከር ለመነሳሳት ምክንያት ሆኖታ ል ።

በአንድ ቦታ ይካሄድ ነበረው ጉባዔ ፤ በሶስቱም ዋና ዋና ከተሞች (አምስተርዳም ፤ ሮተርዳምና ዴን ሃግ) ሰንበት ት/ቤቶች አገልግሎቱ እየተስፋፋ ስለሄደ፤ ከሶስቱም ሰንበት ትምሕርት ቤቶች በተውጣ ጡ ካህናትና ምመናን እ.አ.አ. March 1994 የመጀመሪያው አሰባሳቢ መንፈሳዊ ኮሚቴ ከተማ ተመረ ጠ ።

የተመረጠው መንፈሳዊ ኮሚቴም ፤ የሰብሳቢነቱን ቦታ ዘግይተው በዚያው አመት መጨረሻ ላይ ለሚ መጡት ለአባ አፈወርቅ ጌታነህ በመተው ሌሎች የአገልግሎት ክፍሎችን ተመዳድቦ በመሥራት ላይ እያለ፤ በዓመቱ መጨረሻ ላይም አባ አፈ ወርቅ ጌታነህ ለአገልግሎት ወደ ኔዘርላንድ በመምጣታቸው ኮሚቴው እሳቸውን ሰብሳቢ አድርጎ ፤ ሥራውን ቀጠለ ። በዚሁ ወቅት አካባቢ ቀሲስ ዳዊት ተገኝም መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን መስጠት የጀመሩበት ጊዜ ነበር ።

ኮሚቴውም በሥሩ ፤ የአምስተርዳም ፍኖተ ሰላም ፤ የዴንሃግ ውሉደ ብርሃን ፤ የሮተርዳም ጸሀየ ጽድ ቅ፤ ሰንበት ት/ ቤቶችን ፤ በቫኽኒንገን ፣ በዴልፍትና በኤንስከዴ ዩኒቨርሲቲዎች የግቢ ጉባኤያትን እ ንዲሁም በቤልጅየም ብራስልስ ጽርሃ ጽዮን ሰንበት ት/ ቤትን አቅፎ ፤ በየሳምንቱና፤ በየአስራ አምስ ት ቀኑ እንዲሁም እንዳመቺነቱ በዓበይት በዓላትም ፤ በዚሁ በሚገኙ ካሕናትና ከውጭም ካህናትን በ መጋበዝ የቅዳሴና የስብከተ የወንጌል አገልግሎት እንዲሰጥ በማድረግ መጠነ ሰፊ መንፈሳዊ አገልግሎ ት እንዲሰጥ በማድረግ ፤ በኔዘርላንድ አገር ለተቋቋመችው ቤተ ክርስቲያናችን ዕድገት ታላቅ አስተዋ ጽኦ አበርክተዋል ። ቀደም ሲል የተመረጠው ኮሚቴም ፤ ብዙም ሳይቆይ ስራውን አቁሞ ስለበነበረ ፤ አባ አፈወርቅ የ3 ዓመት ቆይታቸውን ፈጽመው ወደ ኢትዮጵያ ከመመለሳቸው በፊት ፤ የሰበካ ጉባኤ እስከሚቋቋም ድረስ ፡ ከሶስቱም ከተሞች ሰንበት ትምርት ቤቶች የተወከሉ አባላትን ያቀፈ ጊዜያዊ ኮሚቴ በ1996 አጋማሽ ተቋቋመ ። አባ አፈወርቅ ከሄዱ በኋላ ዲ/ን ከፈለኝ ወ/ጊዮረጊሰ የቅስና ስልጣ ን በመቀበላቸው አገልግሎቱ ባለበት ቀጠለ ።

## ክፍል ሁለት

በወቅቱ የምዕራብ አውሮፓ ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ሰላማ ፤ ለሐዋሪያዊ አገልግሎት ከእንግ ሊዝ ወደ ኔዘርላንድ በመጡበት ወቅት አባታዊ ቡራኪና ትምህርት በመስጠት የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ አስገኚ ኮሚቴ እ. አ. አ. September 6 1998 ዓ.ም እንዲቋቋም በማድረጋቸው ለቤተ ክርስቲያኗ መ ንፈሳዊ አገልግሎት እድገት መሠረተ ጥሏል ።

በመቀጠልም የምዕራብ አውሮፓ ሊቀ ጳጳስ ሆነው በብፁዕ አቡነ ሰላማ የተተኩት ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ እ. አ. አ. March 1999 የቅዱስ ገብርኤልን ጽላት ወደ ሆላንድ ይዘው በመምጣት በአምስተር ዳም ከተማ ለተሰበሰው ምእመን ቡራኬና ትምሕርት ከሰጡ በኋላ ፤ ጽላቱን ሆላንድ ለተቋቋመው የኢ ትዮጲያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንዳመጡ በመግለጽ ፤ በአባታዊ ልግስና አበርክተዋል ። ምእመኑም ተረባርቦ ለቅዱስ ገብርኤል ታቦት ማረፊያ የሚሆን ህንጻ ቤ/ ክርስቲያን እንዲገዛ አሳስ በዋል። የቅ/ ገብርኤል ታቦትም በዴንሃ ከተማ ከሚገኘው የራሺያ ገዳም ውስጥ ገብቶ እንዲቀመጥ ተ ደርጓል ።

ሁለቱ ብፁዓን አባቶቻችን የሰጡን አባታዊ ቡራኬያቸውና ምክራቸው ፍሬ አፍርቶ የቤተ ክርስቲያን ባለቤት ለመሆን በመብቃታችን ፤ ቤተ ክርስቲያናችን ውለታቸውን ዘወትር ታስታውሳቸዋለች ።

## ክፍል ሶስት

የቤተ ክርስቲኑኗ ሁለገብ አገልግሎትም ባሉት ካህናትና በጊዜያዊ ኮሚቴው የጋራ ተሳትፎ የተቻለው ን ያህል  ሲካሄድ ከቆየ በኋላ፤ የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳዳሪ የነበሩት የሊቀ ኅሩያን ቀሲስ ከፈለኝ ወ/

ጊዮርጊስ እ.አ.አ. August 2002 ኔዘርላንድን ለቀው ወደ አሜሪካን አገር በመሄዳቸው በአገልግሎቱ
ላይ ችግር ፈጥሮ ነበር ። ይሁን እንጅ በወቅቱ የነበረው ኮሚቴና በሆላንድ ነዋሪ ክሆኑት ዲ/ን (አሁ
ን ቀሲስ) ዳንኤል ፤ ዲ/ን ዮሴፍ ዓለማየሁ ፤ ዲ/ን ተስፉ ለትምህርት የመጡ ዲ/ን መሀሪ መኮንንና
ዲ/ን ኢሳያስ ዓለማየሁ በጋራ ሆነው ምዕመኑን በማስተባበር አገልግሎቱ ባለበት እንዲቅጥል አድርገዋ
ል ።

በመቀጠልም እ.አ.አ. 10 November 2002 ሊቀ ካህናት ቀሲስ ዶ/ ር መርዓዊ ተበጀና ቀሲስ ዳዊት
ተገኝ ባሉበት የመጀመሪያው የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ፤ ቅዱስ ሲኖዶስ ባወጣው የቤተ ክርሰቲያናችን
መመሪያ ቃለ አዋዲ መሰረት ተመርጧል ።

በዚሁ ወቅትም ሊቀ ትጉኃን ሙሉጌታ ስዩም ወደ ኔዘርላንድ ፤ እንዲሁም መልአከ ምሕረት መዝገቡ
ካሣ ወደ ቤልጅየም ለትምህርት በመምጣታቸው ። አዲስ የተመረጠው የሰበካ ጉባዔም ቀሲስ ሙሉጌ
ታ ስዩምን የቤተ ክርስቲያኑ ጊዜያዊ አስተዳዳሪ አድርጎ ፤ በቃለ አዋዲው መመሪያ መሰረት ፤ አገል
ግሎቱን ቀጥሏል ።

የሰበካ ጉባዔው አስተዳደርም፡ ከተለያዩ ድርቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ፤ በአገልግሎት ላይ የሚያ
ጋጥሙ የቤተ ክርሰቲያኗን ነባርና ወቅታዊ ችግሮች መነሻቸውን ለማወቅና ዘላቂ መፍትሄ ለማፈላለግ
የሚረዳ ሁለት ቀን ተኩል የፈጀና ፡ የሰበካ ጉባኤ ፤ የሰንበት ት/ ቤት ኮሚቴ ፤ የሕንጻ ቤ/ክ ኮሚቴ
፤ አባላት እና ከምዕመናንም በተውጣጡ በድምሩ 22 ሰዎች ፡ የተሳተፉበት ሴሚናር በሱስተንበርግ ከ
ተማ እንዲዘጋጅ አድርጓል ።

በሴሚናሩም የቤተ ክርስቲያኗ አጠቃላይ እንቅስቃሴ ፤ በቅደም ተከተል በማንሳት ጠቃሚ ውይይቶች
የጋራ ስምነቶች የተደረጉ ሲሆን ፤ በተለይም የቃል ኪዳኑን (የቅዱስ ገብርኤል) ታቦት ማረፊያና ፤ እ
ንደ ሥርዓታችን አምልኮታችንን የምስፈጽምበት የራሳችን ህንጻ ቤተ ክርስቲያን ሊኖረን የሚችልበት
ን ፤ እንዲሁም በቋሚነት ሊያገለግሉ የሚችሉ ካህን ማምጣት የሚቻልበትን መንገድ ፤ በሰፊው በመ
ወያየት የጋራ ውሳኔዎችን አሳልፏል ።

## በዚህም መሠረት

ሕንጻ ቤተ ክርስቲያንንን በተመለከተ ፤ የሕንጻው ዓይነትና ይዘት…..,.፤ እንዲሁም የአፈላለጉን ዘዴ
ጨምሮ የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳደር ፡ ልምድ ካላቸው ድርጅች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ፤ በጥናት
ላይ የተደገፈ መረጃ እንዲቀርብ እስከዚያው ድረስም ፤ ለሕንጻ ቤተ ክርስቲያን መግዣ ይፈጃል ተብ
ሎ ለሚገመተው የገንዘብ መጠን መነሻ ካፒታሉን ከፍ ለማድረግ ፤ በአንድ ዓመት ውስጥ እስከ መቶ
ሺህ ዩሮ ማሳየት ይቻል ዘንድ ፤ ምዕመኑ በነፍስ ወከፍ በዓመት ውስጥ ተከፍሎ የሚያልቅ 500 (አም
ስት መቶ) ዩሮ እንዲያዋጣ ፤ መክፈል አቅም የሌለውም የሚቻለውን ያህል እንዲከፍል ። በሚል ስ
ምምነት ላይ ተደርሷል ።

የሕንጻ ቤ/ክ ማፈላለጉ ጥናት የሚካሄድበት ቦታን በተመለከተም ፤ ሰፊ ውይይት ከተደረገ በኋላ ፡ ሮ
ተርዳም፤ አምስተርዳም፤ ዴንሃግና ላይደን እንዲሆኑ ተወስኗል ።

ከላይ የተጠቀሱት ቦታዎች የተመረጡበተ ምክንያት ፤ በሶሰቱ ትላልቅ ከተሞች ብዙ ምእመናን ስለ
ሚኖሩ ሲሆን ፤ ላይደን ደግሞ ለሶሰቱመ ከተሞች አማካይ ቦታ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ነ
ው ። ሆኖም ሕንጻ ቤ/ክ እግዚአብሔር በፈቀደበት ቦታ፤ በጥናቱ ውጤትና የምዕመኑና የአባቶች ተሳ
ትፎ እንዲሁም የጋራ ውሳኔን በማጣጣም የሚፈጸም እንዲሆን በዕለቱ የተገኙት የሰሚናሩ ተሳታፊዎች
ተስማምተውበታል ።

ቋሚ አባት ካህን ማመጣትን በተመለከተ ፡ ለጊዜው ሊቀ ቀሲስ ሙሉጌታና ቀሲስ መዝገቡ ሰላሉ፡
አገልግሎቱ በነሱ ስለሚሸፈን ብዙ ችግር ባይኖረውም ፡ ነገር ግን ሁለቱ አባቶች ትምሕርታቸውን
አጠናቀው ብሚመለሱበት ጊዜ ችግር እንዳይገጥመን ፡ ቋሚ ካህን ሊመጡ የሚችሉበት መንገድና
የሚያስፈልጉት (የመኖሪያ ቤት ፡ ደመወዝ እና ሌሎችም) ወጪዎች ከወዲሁ እንዲጠኑ ፡ በማለት
ወስኗል ።

የሰበካ ጉባዔው አስተዳደርም እ.አ.አ. 30 November 2003 አጠቃላይ የምዕመናን ስብሰባ በማድረ
ግ በቤተ ክርስቲያንዋ ልማት ተኮር ሪፖርቱን ያቀረበ ሲሆን፤ የሥራ ዘመኑን ያበቃው የሕንፃ ኮሚቴ
ሪፖርት ካቀረበ በኋላ ፤ ሁለተኛውን ዙር የሕንፃና ልማት ኮሚቴ አባላት አስመርጧል ።

በኔዘርላንድ ደብረ መዊዕ ቅ/ገብርኤል ቤ/ክ ሥር የተቋቋሙትና የሚቋቋሙት ሰንበት ት/ ቤቶችና
ሌሎች ሌሎችም የአገልግሎት ክፍሎች ፤ የሚመሩት በሰበካ ጉባኤው አስተዳደር ሥር ሲሆን ፤
እንደ አስፈላጊነቱ የየራሳቸውን የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ እያወጡ ሰበካው ሲያጸድቅላቸው
ይመሩበታል።

እ. አ. አ. June 13 2004 በAmstelveen ከተማ ለሽያጭ ቀርቦ በነበረው የአይሁዶች የፀሎት ቤት
ውስጥ ለተሰበሰበው ምእመን ፡ ስለ ቤቱ አጠቃላይ ሁኔታ ገለጻ ከተደረገ በኋላ ፤ ምእምኑ የቃል
ኪዳን ሰነድ በመፈረም ክፍያውን በቤተ ክርስቲያናችን የህንጻና የልማት ኮሚቴ የፖስት ባንክ የሂሳብ

ቁጥር ውስጥ እንዲገባ ተደረገው ከፍተኛ ርብርብ ፤ እጅግ አበረታችና ተስፋ ሰጭ ሁኔታዎችን ያመላከተ ነበር ።

በተለያዩ ጊዜያት ወደ ሆላንድ በመምጣት በቅዳሴ በትምህርትና በቡራኬ ያገለገሉ አባቶች

- ከ 1979 ዓ.ም. ጀምሮ ሊቀ ካህናት ዶ/ር መርዓዊ ተበጀ (ከጀርመን ) በተደጋጋሚ፣
- በ 1985 ዓ.ም. ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ፣
- ከ 1987-1990 ዓ.ም አባ አፈወርቅ (አሁን አቡነ ማቴዎስ) ጌታነህ ፣ በቋሚነት
- ቀሲስ ብርሀኑ (ከለንደን፤ በተደጋጋሚ ) ፣
- ቀሲስ ሰለሞን ( ከለንደን፤በተደጋጋሚ ) ፣
- ቀሲስ ደጀኔ ( ከኢትዮጵያ፤ በተደጋጋሚ ) ፣
- ቀሲስ ሰሙ ( ከጀርመን፡ በተደጋጋሚ ) ፣
- ቀሲስ ኮሊን ( ጃማያካዊ የኢ.ኦ.ተ. ቤ/ክርስቲያን ካህን አባት፤ ከለንደን በተደጋጋሚ ) ፣
- ከ 1985-1994 ዓ.ም ዲያቆን ከዚያም ቀሲስ ከፈለኝ ወልደ ጊዮርጊስ በቋሚነት፣
- በሀምሌ ወር 1995 ዓ.ም. ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ ፤ የቤተ ክርስቲያናችን አሁን ስያሜ ፤
  ኔዘርላን ድ የደብረ መዊዕ ቅዱስ ገብርኤል " ብለው ሰየሙ ።
- ሀምሌ 1995 ዓ.ም. አባ ላዕከ ማርያም ( ከጀርመን) ፣
- ሀምሌ 1995 ዓ.ም. ሊቀ ካህናት ብርሀኑ ገ/አማኑኤል (ከኢትዮጵያ) ፣
- ከነሀሴ 1995 ዓ.ም. ጀምሮ አባ ኃ/ገብርኤል ግርማ (ከኢንግላንድ) በተደጋጋሚ ።
- ከ2002 እስከ 2007 ሊቀ ትጉሀን ሙሉጌታ ስዩም በቋሚነት
- ከ2002 እስከ አሁን መልአከ ምሕረት መዝገቡ ካሳ ከቤለጄዬም በተደጋጋሚ ።
- ከከ2005 እስከ አሁን መልአከ ሰላም አባ ተስፋ ማርያም ላቀ በቋሚነት
- በተጨማሪም የቤተ ክርስቲያናችን አገልግሎት በሆላንድ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ፡

ደከመን ሰለቸን ሳይሉ ያለ ምንም ክፍያ በነጣ ሲያገለግሉ የነበሩትና አሁንም ያሉት ዲያቆናት እና ሰባክያነ ወንጌል ለቤተ ክርስቲያናችን እዚህ ደረጃ መድረስ ዓይነተኛ ተጠቃሾቸ ስለሆኑ ምንጊዜም ቢሆን ባለውለታችን ናቸው ።

በመቀጠልም የሰበካ ጉባዔው ፤ በሆላንድ ያለው ምዕመን ስለ ሀይማኖቱና ስለ ቤተ ክርቲያኑ የበለጠ ግንዛቤ ለማስጨበጥ እንዲያስችለው  በማሰብ ፤ ትምህርትና እውቀት ሊያገኝ የሚችልበት ታላቅ ዐውደ ርዕይ (ኤግዚብሽን) ጥቅምት 13 እና 14 1997 ዓ.ም (እ.አ.አ. 23 እና 24 October 2004) በዴንሃግ ከተማ አቅርቧል። ስለ ዐውደ ርዕዩ ይዘት፣ ለመረዳት ላይ ይጫኑት።

በመጨረሻም በቋሚነት ተመድበው በሙሉ ጊዜ የሚያገለገለግሉና የቤተ ክርስቲያኑን አስተዳደር የሚመሩ አባት እንዲመደቡ በሚለው ሀሳብ ላይ የሰበካ ጉባዔው በስፋፋት ከተወያየ በኋላ አሁን በትምሕርት ላይ ያሉት ካሕናት አባቶች የሚያገለግሉት በትርፍ ጊዜያቸው ስለሆነና ትምሕርታቸውን ጨርሰው ሲሄዱ የግድ ቋሚካህን ስለሚያስፈልግ ከአሁኑ ይህን ኃላፊነት ተረክበው ሊመሩ የሚችሉ እና በሥራ ልምድም ሆነ በቤተ ክርስቲያን በቂ ችሎታ ያላቸው አባት ከወዲሁ መፈለግ አለብን በሚለው ሀሳብ ሁሉም አባላት በሙሉ ድምጽ ተስማምተዋል ።

በዚህ መሠረት በተባበሩት ዐረብ ኤምሬትስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ኃላፊና የአቡዳቢ ደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ የሆኑት መልአከ ሰላም አባ ተስፋ ማርያም ላቀ እንዲመጡ በሚለው ሀሳብ የሰበካ ጉባዔ አባላት በሙሉ ድምጽ ወስነዋል ። የተማሙበትና የተፈራርሙበት ደብዳቤም ለቤተ ክሕነቱ ቀርቦ አባ ተስፋ ማርያም ወደ ሆላንድ ተዛውረው ከ April 20 2005 ጀምሮ የኔዘርላድ ደብረ መዊዕ ቅዱስ ገብርኤል አስተዳዳሪ ሆነው ማገልገል ጀምረዋል ።

## ክፍል አራት

ቀደም ሲል የተመረጠው የሰበካ ጉባዔ ፤ ጉባዔ ስብሰባ በቃለ ዓዋዲ ደንብ መሠረት ፤ የሶስት ዓመት የአገልግሎት ዘመኑን ስለአጠናቀቀ ፤ ቀጣይ ምርጫ እንዲደረግ ሰበካ ጉባዔው ከተስማማ በኋላ ፤ የምርጫው ቀንም የካቲት 5 1998 (Feb. 12 2006) እንዲሆንና ምርጫውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሁኔታዎች ከማመቻቸቱ ጎን ለጎን፤ በየሰንበት ት/በቶቹ ለአገልግሎት የሚያዘጋጅ ትምህርት እንዲሰጥ ተወሰነ ። በዚህ መሠረት በሶስቱም የሰንበት ት/ ቤቶች (በአምስተርዳም በዴንሃግና በሮተርዳም) አስመራጭ ኮሚቴዎች እንዲመረጡ ከተደረገ በኋላ ። አስመራጮችም ከየተወከሉባቸው ሶስቱም ሰ/ት/ ቤቶች 15 እጩዎችን መልምለው እንዳጠናቀቁ፤ የካቲት 5 1998 (Feb. 12 2006) በሮተርዳም ፀሀየ ጽድቅ ሰንበት ት/ቤት፤ በሆላንድ አገር የሚገኙ አጠቃላይ ምእመናን በተገኙበት ከሶስቱም ሰንበት ት/ቤቶች የቀረቡት እጩዎች ቀርበው ፤ የምርጫው ሥነ ስርዓት ተካሄዷል ።

የምርጫው ስነ ሥርዓት ከተጠናቀቀ በኋላ ላለፉት ሶስት ዓመታት በሰበካ ጉባዔ አባልነት በተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች ተመድበው ላገለገሉ የሰበካ ጉባዔ አባላት የምስክር ወረቀት ተሰጥቷቸዋል ::

በተጓደሉት አባላት ምትክና በሚያስፈልጉ የአገልግሎት ክፍሎች ከተጠባባቂዎችና ከካህናት የተተኩ አዳዲስ አባላትን ያካተተው ፣ የሰበካ ጉባዔ የሥራ ድልድል የሚከተለው ነው ።

1. አቶ ታዬ ሁሴን................ ም/ሰብሳቢና የሮተርዳም ሰ/ት/ቤት ተወካይ
2. አቶ ዳዊት ናቅአርጋቸው......... ዋና ጸሐፊ
3. ቀሲስ ዳንኤል ይፍሩ.............. ት/ት ክፍል
4. ዲ/ን ዮሴፍ ዓለማየሁ.............. ት/ት ክፍል
5. ዲ/ን ኃይለ ገብርኤል............... የአምስተርዳም ሰ/ት/ቤት ተወካይ
6. ወ/ሮ ገነት ሰብስቤ.................. ሂሳብ ክፍል
7. ወ/ሮ ማሾ ፋንታ..................... የህንፃ ቤተ ክርስቲያን ተወካይ
8. ወ/ሮ ሃይማኖት ዘለቀ............. ገንዘብ ያዥ
9. አቶ ታደሰ ጃራ.................... ቁጥጥር ክፍል
10. ወ/ሮ አሥራት ተክሌ............ የዴንሃግ ሰ/ት/ቤት ተወካይ
11. አቶ ዘሪሁን ሸንቁጤ............. ንብረት ክፍል
12. አቶ አማረ ለይኩን .............. አባል ፣ ናቸው ።

መልአከ ሰላም አባ ተስፋ ማርያም ላቀም ፣ አገልግሎቱንም ሆነ አስተዳደሩን በቋሚነት (በሙሉ ጊዜ) ከተረከቡበት ጊዜ ጀምሮ ፡ ከአዲሱ የሰበካ ጉባዔ ፣ ከሰንበት ትምሕርት ቤት ፣ እና ከህንጻ ኮሚቴ አባላት ጋር በመካከር በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል ።

ከተከናወኑት ተግባራትም ጠቂቶቹ ፤ ቀደም ሲል በነበሩት አምስተርዳም ፣ ሮተርዳምና ዴንሃግ፡ ሰ/ት/ቤቶች ተጨማሪ የወንጌል ትምሕርትና የቅዳሴ መርሃ ግብሮችን አስፋፍቶ አገልግሎቱን ከመቀ ጠል ጋር በኡትሬኽትና ኢንዶቨን ሁለት ጉባዔያትን በማቋቋም ፣ ሰንበት ቤቶችን ወደ አምስት ከፍ እንዲሉ ተደርጓል ።
ተተኪ አገልጋዮችን ከዚሁ ለማፍራት ይቻል ዘንድ ፣ በዴንሃግ ፣ ሁለት ጊዜ ፣ በዴልፍት ግቢ ጉባዔ ሁለት ጊዜ ኮርሰኞች ፣ መሠረታዊ የሃይማኖት ትምሕርትና ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ተምረው ተመርቀዋል ።
በተጨማሪም ፡ በግንባር ከሚያገለግሉና ለክሕነት የሚያበቃ ሥነ ምግባር ያላቸው ሶስት የሰንበት ትምሕርት ቤት ወጣቶችን በማሰልጠን ማዕርገ ዲቁና የተቀበሉ ሲሆን ፣ በዲቁና በማገልገል ላይ የሚገኝ የዲ/ን ዳንኤል የቅስና ማዕርግ መቀበልም ፣ የነበረብን የካሕናት እጥረት በመጠኑም ለማሟላት አስችሎናል ።

## ክፍል አምስት

መንፈሳዊ አገልግሎቱን ከማካሄድ ጎን ለጎንም ፣ የህንጻ ኮሚቴውን በማጠናከር ፣ ምእመናን ፡ ለቤተ ክርስቲያን መግዣ የሚሆን ገንዘብ የሚያደርጉት አስተዋጽኦ እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ ቀደም ሲል በተያዘ ው ዕቅድ መሠረት ፣ የራሳችን የሆነ ቤተ ክርስቲያን ይኖረን ዘንድ ልዩ ትኩረት በመስጠት በተለያ ዩ ከተሞች የሚሸጥ ቤተ ክርስቲያን በማፈላለጉን ተግባር ላይ በሰፊው ተንቀሳቅሷል ።በዚህም መሠረ ት ፡ በደቡብ ሆላንድ ሮተርዳም አካባቢ ፔርኒስ በሚባል ቦታ በተመጣጣኝና ከአቅማችን ጋር ሲተያ ይ ልንገዛው በምንችለው ዋጋ የሚሸጥ ቤተ ክርስቲያን በመገኘቱ ፡ ሁሉም የኮሚቴ አባላት ማለትም የሰበካ ጉባዔ ፡ የህንጻ ኮሚቴና የሶስቱም የሰ/ት/ቤቶች የኮሚቴ አባላት በጋራ ተወያይተው የደረሱበት ን የጋራ ስምምነት ፡ ለሕዝበ ክርስቲያኑ አቅርበው ፣ እንዲገዛ ካስወሰኑ በኋላ ፡ የሀገሩ ህግ በሚፈቅደ ው መሰረት ፡ ከባለሙያዎችና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች ጋር አስፈላጊውን ሁሉ በማሟላት ፣ የግዢው ሂደት ሊጠናቀቅ ችሏል ። ጸሎታችንን ሰምቶ የረጅም ጊዜ ምኞታችን በ መፈጸም የህንጻ ቤተ ክርስቲያን ባለቤት እንድንሆን ላበቃን ለኃያሉ አምላካችን ከፍ ያለ ምስጋናችን ን እናቀርባለን ።
የቤተ ክርስቲያኑ አጠቃላይ ዋጋ 315 000 ዩሮ ሲሆን ፡ ቀደም ሲል በቤተ ክርስቲናችን የህንጻና የል ማት ኮሚቴ ስም በተከፈተው የባንክ አካውንት ተጠራቅሞ ከነበረው 161.000 ዩሮ ላይ የቅድሚያ ክፍ ያ 120 000 ዩሮ ከፍለን ቀሪውን 195 000 ዕዳ ከ 4.25 ጋር በ 11 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ከፍለን እን ድናጠናቅቅ ከተስማማን በኋላ ፡ ከቅድሚያ ክፍያ 120 000 በተጨማሪ ለተለያዩ የሽያጭ ፕሮሰስ ማ ስፈጸሚያዎች ማለትም ለኖታሪስ ፣ ለBTW(ታክስ) ፣ እናም ሌላውን ጨምሮ በድምሩ 140,782.21 ዩ ሮ በመክፈል ተፈራርመን የቤተ ክርስቲያኑን ቁልፍ ተረክበናል ።

ቤተ ክርስቲያኑ በእጃችን እንደገባም ፡ ከሰበካ ጉባዔ ፡ ከህንጻ ኮሚቴና ከሰ/ት/ቤቶች ፡ አባላት የተውጣጣ የቴክኒክ ኮሚቴ በማቋቋም ። የእድሳትና ውስጡንም ሆነ ውጪውን በራሳችን የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት የማስተካከል ሥራው ተጠናቆ ፤ ለቅዱስ ገብርኤል በዓለ ንግሥ ሐምሌ 15 1999 ( 22 2007) በብፁዕ አቡነ እንጦንስ የሰሜን ምዕራብ አውሮፓ ሊቀ ጳጳስ ተባረኮ ቅዳሴ ቤቱ ተከብሯል ።

## ምስጋና

ሥራው ከተጀመረበት ቀን ጀምሮ በምክራችሁ ፡ በሙያችሁ ፡ በጉልበታችሁ ፡ በገንዘባችሁና በምት ችሉት ሁሉ ቅን አገለግሎት ላበረከታችሁ ካሕናትና ምእመናን በሙሉ በእግዚአብሔር ስም ከልባችን እናመሰግናለን ።

## ማሳሰቢያ

በኔዘርላንድ አገርም ይሁን በመላው ዓለም የምትኖሩ ፡ የኢትዮጵያ ኦርቶደክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተ ከታይ የሆናችሁ ክርስቲያን ወገኖቻችን ፡ ይህ የእግዚአብሔር ቤት የሁላችንም ነውና ፡ ቀሪ ዕዳችንን በቶሎ ከፍለን እናጠናቅቅ ዘንድ በጸሎታችሁ ፡ በዕውቀታችሁ ፡ በገንዘባችሁ ፡ እና በምትችሉት ሁሉ ትብብራችሁን ትለግሱን ዘንድ በታላቁ መልአክ በቅዱስ ገብርኤል ስም ጥሪያችንን እናቀርባለን ።

**እግዚአብሔር አምላክ**
**አገልግሎታችንን ይባርክ**

**የኔዘርላንድ ደብረ መዊዕ ቅዱስ ገብርዔል ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባዔ ጽሕፈት ቤት**